Amharic | አማርኛ

መጋቢት 2026

homes victoria

**ታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ**

# የFlemington

ማህበረሰብ ዝመና



**በቦታው ላይ ምን እየሆነ ነው**

### የኢድ በዓልን አብረውን ያክብሩ!

እሑድ 29 ማርች፣ ከሰዓት በኋላ ከ1-5 ሰዓት በ ባንክል ስትሪት ሪዘርቭ (Buncle Street Reserve)፣ ኖርዝ ሜልበርን

### የአየር ማቀዝቀዣ ተከላ

ስራዎች በ 126 እና 130 ሬስኮርስ ሮድ/ Racecourse Road እየቀጠሉ ነው

### የጣቢያ መሠረተ ልማት ስራዎች

በ2026 የመሠረተ ልማት ስራዎችን በአከባቢው በሙሉ እናጠናቅቃለን። እነዚህ ሥራዎች እንደ ኤሌክትሪክ እና ውሃ ያሉ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ይጠብቃሉ። ስራዎች በሚቀጥሉት ሳምንታት ውስጥ ይጀምራሉ።

# እኛ እዚህ ያለነው በ29 ክራውን ስትሪት ላይ ላሉ ነዋሪዎች ነው

ወደ ሌላ ቦታ ከሚዛወሩ ነዋሪዎች ጋር የምክክር መድረክ አሁን ተከፍቷል።

ቤቶች ቪክቶሪያ የአቦርጂናል እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪዎችን የምድሪቱ ባህላዊ ጠባቂዎች አድርገው ይቀበላሉ እና ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎቻቸውን እውቅና ሰጥተዋል እና ያከብራሉ።

## ለ29 ክራውን ስትሪት (Crown Street) ነዋሪዎች የምክክር መድረክ ተከፍቷል



የክራውን ስትሪት ነዋሪዎች አጭር የዳሰሳ ጥናት እንዲያጠናቅቁ ተጋብዘዋል።

ይህ ኦፊሴላዊ የመዛወሪያ ቅጽ አይደለም። ወደ ሌላ ቦታ በሚዛወሩበት ጊዜ የህብረተሰቡን ፍላጎቶች ለማቀድ ብቻ ይረዳናል።

ደብዳቤዎች፣ ኢሜይሎች እና የጽሑፍ መልእክቶች ከልዩ ኮድ ጋር ተልከዋል።

የዳሰሳ ጥናቱን ድረ-ገጽ ይጎብኙ እና ልዩ ኮዱን እስከ **ማርች 27 ቀን 2026 12 ሰዓት ከቀትር በኋላ** ድረስ ያስገቡ።

የዳሰሳ ጥናቱን በመስመር ላይ ያጠናቀቁ ነዋሪዎች **ከ10 የ200 ዶላር የስጦታ ቫውቸሮች አንዱን** በውልዎርዝ (Woolworths)፣ ቢግዳብሊው (BigW) ወይም በተሳታፊ ኢጂ አምፖል ነዳጅ (EG Ampol Fuel) ማደያ ቦታዎችች ላይ የሚያወጡት የስጦታ ቫውቸር የማግኘት እድል አላቸው።

የQR ኮድን ስካን ያድርጉ ወይም **homes.vic.gov.au/ relocations-survey** ን ይጎብኙ

| እዚህ ያለነው ጥያቄዎቻቹ ለመመለስ ነው። | የማህበረሰቡን ፍላጎቶች ለመረዳት እርስዎን ማዳመጥ። | **ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ተሳትፎ** | | | መዛወር የድጋፍ እና የማዛወር ማዕከሎች ተከፍተዋል። | **ተከራዮች ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር ይደገፋሉ** | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጥር 2026 | ፌብርዋሪ 2026 | ማርች 2026 | አፕሪል 2026 | ሜይ 2026 | ጁን 2026 | ጁላይ 2026 | ፌብርዋሪ 2028 |

## እንደተገናኙ መቆየት

**የመረጃ ክፍለ ጊዜያት**

**የምክክር አስተያየት**

**ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት መመዝገብ**

ተሳታፊ ሆኖ ለመቆየት ከታች ያለውን ይጎብኙ፦

homes.vic.gov.au/flemington-precinct




በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ **Homes Victoria** ብለው በመፈለግ ይከተሉን

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place፣ Melbourne።
© የቪክቶሪያ ግዛት፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ ማርች 2026። (HV007326)።
በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 የታተመ።

More Homes For Victorians

VICTORIA State Government

# በፍሌምንግተን ውስጥ ምን እየሆነ ነው

መጋቢት 2026



### ሆላንድ ኮርት 286 አዳዲስ ቤቶች እና የህዝብ መናፈሻ

**ስራ በሂደት ላይ ነው**

- በመጀመሪያዎቹ አፓርታማዎች የጥራት ፍተሻ በመካሄድ ላይ ነው
- በሕዝብ መናፈሻ ላይ ስራዎች እየተጀመሩ ነው

### 12 ሆላንድ ኮርት (Holland Court)

**ህንጻዎችን መጠበቅ**

- ክፍት አፓርታማዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ ማድረግ
- ከባዶ አፓርታማዎች፣ ኮሪደሮች እና የአሳንሰር ቦታዎች እና ከህንጻው ውጭ ካሉ ቦታዎች ላይ ትናንሽ የቁሳቁስ ናሙናዎችን መውሰድ
- ቁም ሣጥኖችን፣ የወለል ንጣፎችን እና ሌሎች ትናንሽ እቃዎችን ከባዶ አፓርታማዎች ማስወገድ
- ለሠራተኞች ጊዜያዊ መገልገያዎች ይዘጋጃሉ

**የመኪና ማቆሚያ መዘጋት**

- በ12 ሆላንድ ኮርት አቅራቢያ ያሉ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የመኪና ማቆሚያዎች በአካባቢው ያሉ ስራዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ እንድንሰራ ለማስቻል አሁን ተዘግተዋል




### 126 እና 130 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

**የኤሌክትሪክ ስራዎች**

- በቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶች ላይ የኤሌክትሪክ ስራዎች ቀጥለዋል

**በ126 ሬስኮርድ ሮድ ላይ የአየር ኮንዲሽነር ተከላ እየቀጠለ ነው**

### 120 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

**ህንጻዎችን መጠበቅ**

- ክፍት አፓርታማዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ ማድረግ
- ከባዶ አፓርታማዎች፣ ኮሪደሮች እና የአሳንሰር ቦታዎች እና ከህንጻው ውጭ ካሉ ቦታዎች ላይ ትናንሽ የቁሳቁስ ናሙናዎችን መውሰድ

### ጥቃቅን የመንገድ ስራዎች

- በሆላንድ ኮርት ላይ በጠርዝ እና በእግረኛ መንገድ ላይ የተደረጉ ለውጦች
- የእግረኛ መንገድ እና አንዳንድ መኪና ማቆሚያዎች ለአጭር ጊዜ ይዘጋሉ
- ተሽከርካሪዎችን እና እግረኞችን ለመምራት የትራፊክ አስተዳደር ይደረጋል

### የጣቢያ መሠረተ ልማት ስራዎች

- ጣቢያው እየተገነባ ሲሄድ ስራዎች የኤሌክትሪክ እና የውሃ መስመሮች ከአዳዲስ ሕንፃዎች ጋር በቀላሉ መገናኘታቸውን ያረጋግጣሉ
- በመጪዎቹ ሳምንታት ሥራ ይጀመራል ይህም እስከ 2026 መጨረሻ ድረስ እንዲቀጥል ታቅዷል
- መቆራረጥን ለመቀነስ በየደረጃው ይከናወናሉ
- የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ ምልክቶች እና መለያዎች ይደረጋሉ
- የቤቶች መዳረሻ እንዳሉ ይጠበቃል፣ ነገር ግን ተለዋጭ መንገዶች አንዳንድ ጊዜ ሊኖሩ ይችላሉ
- ስራው ሲጀመር ምን ማድረግ እንዳለቦት ለማወቅ የሚሰጠውን መረጃ ይከታተሉ

N

ስራችን የሚመራው በምክር ቤትዎ መደበኛ የስራ ሰዓታት ነው፦

**ከሰኞ እስከ አርብ**
ከ7am እስከ 6pm

**ቅዳሜ**
ከ9am እስከ 3pm

ተጨማሪ መረጃ ለሚፈልጉ ነዋሪዎች የአካባቢዎን የመኖሪያ ቤቶች ቢሮን ያነጋግሩ፦

**1300 360 462**

**ascotvale.housing@dffh.vic.gov.au**

አንዳንድ ጊዜ ከእነዚህ ሰዓታት ውጭ ለመስራት የምክር ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል ነገርግን ይህ ከተከሰተ ነዋሪዎችን እናሳውቃለን።

ሁሉም ስራዎች በከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎች እና ህጋዊ መስፈርቶች ይከናወናሉ።

## የመልሶ ማልማት ስራዎች የጊዜ ሰሌዳ

12 ሆላንድ ኮርት (Holland Court) እና 120 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

**ነዋሪዎች በእነዚህ ሕንፃዎች ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ምንም ዓይነት ማፍረስ አይደረግም።**

**2025**

### 1. የበለጠ ማወቅ እና ነገሮችን ደህንነታቸው የተጠበቀ ማድረግ

- ክፍት ባዶ አፓርታማዎችን ደህንነታቸው የተጠበቀ ማድረግ
- ቁሳቁሶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስተዳደር ጣቢያውን እና ህንጻዎችን መመርመር
- መደበኛ ጥገናን መቀጠል

**2026፦ እዚህ ነን**

### 2. ዝግጁ መሆን

- ለደህንነት ሲባል ጣቢያ እና ምልክት ማዋቀር
- የአገልግሎት ግንኙነቶችን መፈተሽ
- ለእግረኞች፣ ለመኪናዎች እና ለመኪና ማቆሚያ ጥቅም በሚውልበት ወቅት ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ
- ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በህንፃዎች ውስጥ እየሰራን ነው
- ቁም ሣጥኖችን፣ የወለል ንጣፎችን እና ሌሎች ትናንሽ እቃዎችን ከባዶ አፓርታማዎች ማስወገድ

### 3. ፈረሳ

- ስካፎልዲንግ/ መወጣጫ መትከል
- ጥንቃቄ በተሞላበት ደረጃዎች ግንባታን ማፍረስ
- መደበኛ የማህበረሰብ መረጃዎች

በቋንቋዎ ውስጥ መረጃን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ይጎብኙ - **homes.vic.gov.au/information-in-your-language**

ለአጠቃላይ ጥያቄዎች የኢሜይል ኣድራሻ፦

**enquiries@homes.vic.gov.au**